የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራሦስተኛ ዓመት ቁጥር ፲፪
አዲስ አበባ ጥር ፲፬ ቀን ፲፱፻፺፱

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

13th Year No. 12
ADDIS ABABA 22nd January, 2007

## ማ ው ጫ

አዋጅ ቁጥር ፭፻፲፪/፲፱፻፺፱ ዓ.ም

ለገጠር የኤሌክትሪክ አቅርቦት ማስፋፊያ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ብድር ከዓለም ዐቀፍ የልማት ማኅበር ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂ ያአዋጅ…. ገጽ ፫ሺ፭፻፳፪

## CONTENTS

**Proclamation No. 512/2007**

International Development Association Loan Agreement for Electricity Access (Rural) Expansion Project Ratification Proclamation …. Page 3522

## አዋጅ ቁጥር ፭፻፲፪/፲፱፻፺፱

## በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በዓለም ዐቀፍ የልማት ማኅበር መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ

ለገጠር የኤሌክትሪክ አቅርቦት ማስፋፊያ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል መጠኑ ፺፪ሚሊዮን ፰መቶ ሺህ ኤስ.ዲ.አር (ዘጠና ሁለት ሚሊዮን ስምንት መቶ ሺህ ኤስ.ዲ.አር) የሆነ ገንዘብ የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በዓለም ዐቀፍ የልማት ማኅበር መካከል እ.ኤ.አ. ኦገስት ፯ ቀን ፪ሺ፮ በአዲስ አበባ የተፈረመ በመሆኑ፤

ይህንኑ የብድር ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ታህሣሥ ፲፪ ቀን ፲፱፻፺፱ ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ ያፀደቀው ስለሆነ፤

በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ ፶፭/፩/ እና /፲፪/ መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "ለገጠር የኤሌክትሪክ አቅርቦት ማስፋፊያ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ብድር ከዓለም ዐቀፍ የልማት ማኅበር ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፭፻፲፪/፲፱፻፺፱" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

## PROCLAMATION NO. 512/2007.

## A PROCLAMATION TO RATIFY THE LOAN AGREEMENT BETWEEN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE INTERNATIONAL DEVELOPMENT ASSOCIATION

**WHEREAS,** a Loan Agreement, between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the International Development Association stipulating that the International Development Association provide to the Federal Democratic Republic of Ethiopia a loan in an amount not exceeding SDR 92,800,000 (ninety two million eight hundred thousand SDR) for financing Electricity Access (Rural) Expansion Project, was signed in Addis Ababa on the 7th day of August 2006;

**WHEREAS,** the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified said Loan Agreement at its session held on the 21st day of December, 2006;

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 55 Sub-Articles (1) and (12) of the Constitution, it is hereby proclaimed as follows:

### 1. Short Title

This Proclamation may be cited as the "International Development Association Loan Agreement for Electricity Access (Rural) Expansion Project, Ratification Proclamation No.512/2007."

## ፪. የስምምነቱ መጽደቅ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በዓለም ዐቀፍ የልማት ማኅበር መካከል እ.ኤ.አ. ኦገስት ፯ ቀን ፪ሺ፮ በአዲስ አበባ የተፈ ረመው ቁጥር 4200ET የብድር ስምምነት ፀድቋል፡፡

## ፫ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስትሩ ሥልጣን

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስትሩ በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ፺፪ሚሊዮን ፰መቶ ሺህ ኤስ.ዲ.አር (ዘጠና ሁለት ሚሊዮን ስምንት መቶ ሺህ ኤስ.ዲ.አር) በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል፡፡

## ፬. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ጥር ፲፬ ቀን ፲፱፻፺፱ ዓ.ም**

**ግርማ ወልደጊዮርጊስ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

## 2. Ratification of the Agreement

The Loan Agreement No.4200ET signed in Addis Ababa on the 7th day of August 2006 between the Federal democratic Republic of Ethiopia and the International Development Association is ratified.

## 3. Power of the Minister of Finance and Economic Development

The Minister of Finance and Economic Development is hereby Empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the loan amount of SDR 92,800,000 (ninety two million eight hundred thousand SDR) in accordance with the terms and conditions set forth in the Loan Agreement.

## 4. Effective Date

This Proclamation shall come into force up on Publication in the Federal Negarit Gazeta.

**Done at Addis Ababa, this 22nd day of January, 2007**

**GIRMA WOLDEGIORGIS**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**